የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian Peoples Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

ሚያዝያ 9 2007 ዓ.ም

ከኢሕአፓ ወክንድ የተሰጠ መግለጫ

ደቡብ አፍሪካ በስደተኞች ላይ የሚደረገውን ጭፍጨፋ እናወግዛለን

ደቡብ አፍሪካ ነፃነቷን ከተቀዳጀች በኋላ በተለያዩ ጊዜያት ሀገር ውስጥ በገቡ ዕና በላባቸው ጥረው ግረው በሚኖሩ ሰላማዊ አፍሪካውያን ስደተኞች ላይ የተለያዩ ዘረፋዎችና ነብስ ግድያዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል፡፡ አሁን ደግሞ ይባስ ብሎ የሰውን ልጅ ከነ ህይወቱ በእሳት ሲቃጠል መንግስትና ህግ ያለበት ሀገር እሰከማይመስልም ድረስ በገጀራ ተጨፍጭፎ ሲገደል ማየት ለህሊና የሚዘገንን አረመኔ ተግባር ነው፡፡
እጅግ የሚያሳዝነው ደግሞ ይህንን ኢ-ሰብዓዊ ተግባር እየፈፅሙ ያሉ የሀገሪቱ ዜጎች ትናንት በፀረ-አፓርታይዱ ትግል ከጎናቸው በመቆም ከኔልሰን ማንዴላ ጀምሮ እስከ የአፍሪካ ብሄራዊ ኮንግረስን ተዋጊ ክንፍ በማሰልጠን፣ እንዲሁም በዲፕሎማሲው ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረጉትንና ለነፃነት ትግላቸው ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉትን ሁሉ ዋጋ የሚያሳጣ ውለታ ቢስ መሆንም ጭምር ነው ::

የደቡብ አፍሪካ ህዝብና መንግስት ይህንን አረመኔያዊ እና ህገ ወጥ ተግባር በአስቸኳይ እንዲያስቆም እየጠየቅን፣ ይህንን በፈፀሙት ላይ መንግስት በአስቸኳይ ተገቢውን ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ በጥብቅ እናሳስባለን፡፡ የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት በየትኛውም ቦታ በሰው ልጆች ላይ የሚደርስን ኢ-ሰብዓዊና አረመኔያዊ ድርጊት በጥብቅ ያወግዛል፡፡

ፍትህና ሰላም ወዳድ ዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ይህን ኢሰብአዊ ድርጊት እንዲያወግዙም ጥሪውን ያቀርባል

Tel: 202-291-5832 5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011
E-mail: eprpylnew @gmail.com Website: www.eprpyl.com